


## ምንም እንኳ ሀውልት ባናቆምላቸው
(አንሙት ከለንደን)

ቃል ሰው ሆነ ብሏል፣
ጠሊቅ ነው ምስጢሩ፣
ገድሉ ነው የበዛ፣
ገደብ የለው ቁጥሩ፣
ያንን የሰው ቤዛ፣
ልኩን ለመወሰን አትገዳደሩ፣
አእላፍ ኢየሱሶች፣
በፈፋ፣ በሜዳ፣ በየሸንተረሩ፣
ሰውን ለመታደግ መስዋዕት እየሆኑ፣
አሉ፣ ይኖራሉ፣ በፊትም ነበሩ።

ምንም እንኳ፣ ሀውልት ባናቆምላቸው፣
ሳናይ፣ ሳንሰማቸው፣
ሞታችንን ሞተው፣
የምንኖርባቸው፣
ለእኛ መኖር ግብር፣ ጭዳ ያረግናቸው
ምድር ብራናቸው፣
ብዕር አጥንታቸው፣
ቀለሙ ደማቸው፣
ጸሐፊ ስራቸው፣
እየሆነላቸው፣
ዝክረ-መታሰቢያ፣ የማንነታቸው፣
የተፃፈላቸው፣ የሚፃፍላቸው፣
የሰው ልጅ ቤዛዎች፣
የምድር ኢየሱሶች፣
እጅግ ብዙ ናቸው፣
ምንም እንኳ ሀውልት ባናቆምላቸው!

(በየፈፋው ለወደቁ ሕዝባዊ ሰማዕታት መታሰቢያ)
ህዳር 14 ቀን 2002 ዓ. ም.